## ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ የሕግ አወጣጥ ሥርዐት

## ክፍል ሁለት

## የሕግ አወጣጥ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት ፡ ትንታኔና ሀሳብ ።

* ሺፈራው ወልደሚካኤል

የሕግ አወጣጥ ሂደት የጽሑፍ ሕገ መንግሥት ባላቸው አገሮች በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ሳይጠቀስ አይታለፍም ። የሕግ አወጣጥ ሂደቱ ማመንጨትን ፡ መደንገግን ፡ መፈረምንና በነጋሪት ጋዜጣ ማሳተምን ያካትታል ። በአንዳንድ አገሮች የሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ አንዱ ሌላው ጠቃሚ ደረጃ ከለሳና ቅንብር የሚባለው ይገኝበታል ።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የካቲት 1979 ዓ ም በውሳኔ ሕዝብ በጸደቀው የኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት ውስጥ የሕግ አወጣጥ ሂደትን የሚመለከቱ አንቀጾችን ለመመርመርና የዚህን ሂደት ደረጃዎችም አጢኖ ምናልባትም በዚሁ ሕግ ያልተጠቀሱ ነገሮች ቢኖሩ እንደማሚያ የሚያገለግሉ አንዳንድ ሀሳቦችን ለመሰንዘር ጭምር ነው።

### ሕግ ማመንጨት ።

የሕግ ማመንጨት ደረጃ በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ ቀዳሚ ነው ። የኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 71 ይህንን ይመለከታል ። በዚህ አንቀጽ መሠረት ሕግ የማመንጨት መብት ያላቸው የሚከተሉት ናቸው ።

- የመንግሥት ምክር ቤት
- የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት
- የብሔራዊ ሸንጐ ኮሚሺኖች
- የብሔራዊ ሸንጐ አባሎች
- የሚኒስትሮች ምክር ቤት
- ጠቅላይ ፍርድ ቤት
- ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
- የአስተዳደር ክልሎችና የራስ ገዝ ክልሎች ሸንጐዎች እና
- ሕዝባዊ ድርጅቶች በብሔራዊ አካሎቻቸው አማካይነት ።

ሕግ የማመንጨት መብት አንድ ሕግ እንዲወጣ ሃሳብ የማቅረብ መብት ማለት አይደለም ። ምክንያቱም ይህንን ሀሳብ በአንቀጽ 71 በሰፊው ከተዘረዘሩት ውስጥ ያልተጠቀሰ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ሊያቀርብ ይችላል ና ። ይልቁንም ሕግ የማመንጨት መብት ሕግ መደንገግ ለሚችል አካል ይኸውም ለብሔራዊ ሸንጐ ፡ ለመንግሥት ምክር ቤት ፡ ለሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት ወይም ለሚኒ

ስትሮች ምክር ቤት ረቂቅ ሕጉን ማቅረብ መቻል ማለት ነው ። ለምሳሌ ስለአካባቢ ደህንነት ሕግ እንዲወጣ ፍላጐት ያለው አንድ ግለሰብ የአካባቢን ደህንነት የሚያስጠብቅ ረቂቅ ሕግ ሊያቀርብ ይችላል ። ነገር ግን ግለሰቡ ይህንን የረቂቅ ሕግ ሀሳቡን በብሔራዊ ሸንጎ አጀንዳ ውስጥ እንዲያዝለት ለማቅረብ በሕገ መንግሥት የተሰጠ መብት የለውም ። ቢሆንም ይህ ግለሰብ ይህን ረቂቅ ሕግ በኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 71 መሠረት ሕግ ለማመንጨት መብት ከተሰጣቸው አካሎች ውስጥ ለአንደኛው በማቅረብና ይህንን ረቂቅም የተባለው ባለመብት አካል ካመነበትና ከተቀበለው ረቂቅ ሕጉ እንዲደነገግ ሕግ ለማውጣት በሕገ መንግሥቱ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማቅረብ ይችላል ።

የመነጨው ሕግ ዓይነት በሸንጐ የሚወጣ ከሆነ አዋጅ [1] ፤ በመንግሥት ምክር ቤት ከሆነ ድንጋጌ [2] ወይም ልዩ ድንጋጌ [3] ፡ እንዲሁም በሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት ከወጣ የፕሬዚዳንቱ ድንጋጌ [4] ሊባል የሚችል ዓይነት መሆን አለበት ። ልዩ የፕሬዚዳንቱ ድንጋጌ (አንቀጽ 87 (2) ሹመትን ብቻ የሚመለከት ስለሆነ ይህ ጽሁፍ አይመለከተውም ። የመነጨው ሕግ በሕገ መንግሥቱ መብት በተሰጣቸው አካላት እንደ ደንብ ሆኖ ሊወጣ ይችላል ።

### መደንገግ ፤

በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ የመደንገግ ደረጃ የሚባለው ረቂቅ ሕግ ለማጽደቅ ሥልጣን ባለው አካል ይኸው ረቂቅ ሕግ የሚጸድቅበትና ሕግ የሚሆንበት ደረጃ ነው ። በኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት መሠረት የአንዳንድ ሕጐች የድንጋጌ ሁኔታ ቁልጭ ብሎ የተቀመጠ ሲሆን የአንዳንድ ዓይነት ሕጐች አደነጋገግ ግን ግልጽ አይደለም ።

በኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት የሕጐች ዓይነት ተዘርዝሮ የተቀመጠ ቢሆን ኖሮ ምናልባት ይህ አርእስት በደንብ ተብራርቶ በተተነተነ ነበር ። በተዋረድ ሲታዩ የሕግ ዓይነቶች እንደሚከተለው ሊቀመጡ ይችላሉ ።

| የሕግ ዓይነት | አውጪው አካል |
|---|---|
| አዋጅ | ብሔራዊ ሸንጐ |
| ድንጋጌ | የመንግሥት ምክር ቤት ፣ የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት |
| ደምብ | የሚኒስትሮች ምክር ቤት |
| አዋልድ ደንቦች | ሥልጣን የተሰጠው አካል |

ከላይ ካለው የሕጐች ዝርዝር ውስጥ የሚታየው ግልጽ ግድፈት የመንግሥት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ አለመኖሩ ነው ። ይህም ሕግ የሚወጣው በመንግሥት ምክር ቤት ሲሆን የሚወጣበትም ጊዜ ብሔራዊ ሸንጐ በጉባኤ ላይ በማይቀመጥበት ጊዜና ከስሙ እንደሚታየው “ ልዩ ሁኔታ ” በሚኖርበት ጊዜ ነው ። ልዩ ድንጋጌው የጸና ሆኖ የሚቆየው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ለሚቀጥለው የብሔራዊ ሸንጐ ጉባኤ እስከሚቀርብበት ድረስ ያለውን ጊዜ ያካትታል ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ልዩ ድንጋጌው ከፍተኛው የመንግሥት ሥልጣን አካል በሚያወጣው አዋጅ ላይ እንኳ የበላይነት ይኖረዋል ። ልዩ ድንጋጌው ለብሔራዊ ሸንጐው ከቀረበ በኋላ ወይ በሸንጐው ተቀባይነት ያጣና ሕግ መሆኑ ይቀራል ወይም ደግሞ ተቀባይነት ያገኝና በብሔራዊ ሸንጐው አማካይነት በአዋጅ መልክ ይወጣል ።

ከላይ በተመለከተው የሕጐች ዝርዝር ውስጥ ሌላው ያልተጠቀሰው የሕግ ዓይነት ደግሞ የፕሬዚዳንቱ ልዩ ድንጋጌ ነው ። የፕሬዚዳንቱን ልዩ ድንጋጌ የማ ውጣት ሥልጣን የሚመነጨው ከሕገ መንግሥት አንቀጽ 87 ነው ። ይህን ሥል ጣን መጠቀም የሚቻለው ሸንጐው በጉባኤ ላይ በማይኖርበት ጊዜ ብቻ ነው ። የፕ ሬዚዳንቱ ልዩ ድንጋጌ በብሔራዊ ሸንጐ የተመረጡ ባለሥልጣኖች በፕሬዚዳንቱ መሾማቸው ወይም መሻራቸው ለሕዝብ የሚገለጽበት " ሕግ " ነው ። በአጠቃ ቀሙ አነስተኛነትና በተደጋጋሚ በሥራ ላይ የማይተረጐም በመሆኑ በዝርዝር አልመለከተውም ።

በመሠረቱ አዋጆች በብሔራዊ ሸንጐ ነው የሚታወጁት ። የመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌ ና ልዩ ድንጋጌ በመንግሥት ምክር ቤት ነው የሚታየወጁት ። የፕ ሬዚዳንቱ ድንጋጌ ደግሞ በፕሬዝዳንቱ ነው የሚታወጀው ። የደንቦች በአዋጅ መነ ገር ግን እላይ እንደ ተነጋገርንባቸው ሕጐች በአዋጅ መነገር ዐይነት ግልጽ ሆኖ አይገኝም ።

ደንብ የሚለው ቃል የተወሳው በሕገ መንግሥቱ በሁለት አንቀጾች ውስጥ ብቻ ነው ። በሁለቱም አንቀጾች ውስጥ ቃሉ የተነሳው ለመንግሥት አካሎች ከሚ ሰጥ ሥልጣን ጋር በተያያዘ መልክ ነው ። መጀመሪያ የተነሳው በአንቀጽ 82/1/ ሐ/ ላይ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ አንቀጽ 92/1/ ላይ ነው ። " ተጠሪነታቸው ለብ ሔራዊ ሸንጐ የሆኑ የመንግሥት አካላት የሚያወጧቸውን ደንቦች ለመሻር . . . " የሚያስችል ሥልጣን አንቀጽ 82/1/ ሐ/ ለመንግሥት ምክር ቤት ይሰጣል ። የዚ ህን ንዑስ አንቀጽ ሁለንተናዊ መልኮች ለማየት ሙሉ ምርምር ከማካሄዳችን በፊት ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑት የመንግሥት አካሎች የትኞቹ እንደሆኑ በመጠኑ ማየት ተገቢ ነው ። ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑ የመንግሥት አካሎች (ከመንግሥት ምክር ቤትና ከሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት በቀር) የሚከተሉት ናቸው ።

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት
2. ጠቅላይ ፍርድ ቤት
3. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ
4. ብሔራዊ የሥርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴ
5. የጠቅላይ (የዋናው) ኦዲተር ጽ/ቤት
6. የአስተዳደርና ራስ ገዝ ክልሎች ከፍተኛ ሸንጐዎች ።

ከእነኝህም ውስጥ ሁለቱ አካሎች ማለትም ብሔራዊ የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚ ቴና (በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው የሚል አቋም ካልተወሰደ በቀር) የጠቅላይ ኦዲተር ቢሮ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 71 ሕግ የማመንጨት ሥ ልጣን አልተሰጣቸውም ። ከዚህም በላይ በአንቀጽ 63/3/ ሠ/ እና /ረ/ እና 64/ሠ/ ብሔራዊ የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴና የጠቅላይ ኦዲተር ቢሮ አመሠራረትና የኃላፊዎቻቸው " አመራረጥ " ከመጠቀሱ በቀር ስለሥልጣናቸው ጭራሽ የተ ጠቀሰ ነገር የለም ።

ከዚህ በላይ በተዘረዘረው መሠረት ጥሬ ሀሳቡን ካየን በኋላ ወደ ዋናው ጥያ ቄያችን ማለትም ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑ ሁሉም የመንግሥት አካ

ሎች ደንብ የመደንገግ ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም የሚለውን ነጥብ እን መልከት ።

እስቲ ወደ አንቀጽ 82/1/ ሐ/ እንመለስ ። የዚህ አንቀጽ ዋነኛ ምናልባትም ብቸኛ ዓላማ ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑ የመንግሥት አካላት የሚያ ወጧቸውን ደንቦችና መመሪያዎች ለመሻር የሚያስችል ሥልጣን ለመንግሥት ምክር ቤት ለመስጠት ነው ። እንዲህ ሲባል ደግሞ ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸ ንጐ የሆነ ማናቸውም የመንግሥት አካላት ደንቦች የማውጣት ሥልጣን አላቸው ማለት አይደለም። ነገር ግን መብት ያላቸው እንደነኝህ ያሉት አካላት የሚያወጧቸ ውን ደንቦች የመንግሥት ምክር ቤት ለመሻር መብት አለው ማለት ነው። ይህ ንዑስ አንቀጽ ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑ አካላት ደንቦችና መመሪያዎችን ሊያወጡ እንደሚችሉ አድርጐ ይቆጥራቸዋል ማለት ይቻላል። ስለዚህም በትክክል ለማጠቃለል ያህል ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ ለሆኑ አካላት ደንብ እንዲ ያወጡ የሚያስችል ሥልጣን ይህ አንቀጽ አይሰጣቸውም ።

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 92/1/ በሕግ መንግሥቱ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ደ ንብ የሚለው ቃል የሚገኝበት በዚህ ጉዳይ ላይ እንደሚከተለው ይነበባል ።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል ፣

1\. . . . ደንቦችና መመሪያዎች ማውጣት ፤

በሌላ በኩል ደግሞ አንቀጽ 97 2/ ን ብንመለከት የአስተዳደራዊና ራስ ገዝ ክል ሎች ሸንጐዎች መመሪያዎችን ብቻ ለማውጣት ሥልጣን አላቸው ።

ስለዚህ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ለማውጣት ሕገ መንግሥታዊ ሥል ጣን ሲኖረው የአስተዳደራዊና ራስ ገዝ ክልሎች ሸንጐዎች ግን ይህ ሥልጣን የላ ቸውም ። አንቀጽ 82/1/ ሐ/ ለአስተዳደራዊና ራስ ገዝ ክልሎች ሸንጐዎች መመ ሪያ እንዲያወጡ ሥልጣን ይሰጣቸዋል ብሎ ለመከራከር መሞከር (በአንቀጽ 97/2/ መሠረት እንኳ ቢሆን/ አንቀጹ እንዲሰጥ የማይጠብቀውን ወይም የማያስበውን ነገር እንዲሰጥ ማሰብ ማለት ነው ።

ሌሎቹ የመንግሥት አካላትም ማለትም ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፡ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ ፡ ብሔራዊ የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴና የጠቅላይ ኦዲተር ቢሮ ልክ እንደአስተዳደራዊና ራስ ገዝ ክልሎች ከፍተኛ ሸንጐዎች ሁሉ ደንብ የማውጣት ሕግ መንግሥታዊ ሥልጣን የላቸውም ።

በተቃራኒው በኩል ደግሞ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አካላት መብቶች በሙሉ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተጠቀሱ ቢሆን ኖሮ ስለደንብ አወጣጥ አንድ አንቀጽ ይኖር ነበር ብሎ መከራከር ይቻላል ። ይህ እንደገማቹ ሁኔታ እየታየ ግምት ብቻ —የተሳሳተ ወይም ጥሩ ዓይነት— ሊሆን ይችላል ።

ወደ ሌላ ነጥብ ከመሻገራችን በፊት በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተጠቀሰው " ደንብ " የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ እናብራራ ። በተዋረድ ሲታይ አ ዋጅ ከመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌ ወይም ከሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት ድንጋጌ ይልቅ በበላይነት ደረጃ ላይ ይገኛል።ቢሆንም ሁለቱም የበላይ ሕጐች ናቸው ። በተ መሳሳይ ሁኔታም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 92/1/ እንደተጠቀሰው ደንብ ምንም እንኳ በተዋረድ ሲታይ ከሌሎቹ የበላይ ሕጐች በሞላ የበታች ቢሆንም በደረጃው ግን ቀዳማዊ ሕግ ነው ።

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 92/1/ መሠረት የሚወጡ ደንቦች አዋልድ ደንቦች
አይደሉም ። ደንቦች የሚለው ቃል ትርጉሙ አዋልድ ደንቦች ወይም የበላይ ከሆኑ
ሕጐች ማለትም ከአዋጅ ወይም ከመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌ ላይ የተመሠረቱ
የአፈጻጸም ሕጐች ለማለት ቢሆን ኖሮ ምንም አንቀጽ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ
ባላስፈለገ ነበር ። ይህ ጉዳይ በተሻለ ሁኔታ ሊታይ የሚችለው የአፈጻጸም ሕግ እን
ዲወጣ ሥልጣን በሚሰጠው ቀዳማዊ ሕግ ውስጥ ነው ።

ደንቦች የሚለው ቃል በአንቀጽ 82/1//ሐ/ እና በአንቀጽ 92/1/ ውስጥ አንድ
ዓይነት ይዘት አለው ብሎ መገመት ስህተት ነው ። የብሔራዊ ሸንጎ ፣ የመንግሥት
ምክር ቤት ወይም የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚያወጧቸውን ሕጐች የሚቃረኑ ማና
ቸውንም ደንቦች (አዋልድ ይሁኑ ወይም ሌላ) ለመሻር የሚያስችል ሥልጣን በመ
ንግሥት ምክር ቤት ሥልጣን ክልል ውስጥ ይወድቃል ። ማንኛውም ሕግ ከሕገ
መንግሥቱ ጋር ተቃራኒ መሆን አለመሆኑን የሚወስንና ከላይ በተዘረዘሩት አካላት
ላይ የበላይነት ያለው አካል መደበኛ ስብሰባውን በዓመት አንድ ጊዜ ከሚያካሂ
ደው ከብሔራዊ ሸንጎ በቀር ሌላ ማንም የለም ። በተጨማሪም የመንግሥት ም
ክር ቤት ሕገ መንግሥቱንና ሌሎች ሕጐችንም ጭምር ለመተርጐም ሥልጣን
የተሰጠው አካል በመሆኑ (አንቀጽ 82/1/ ለ/) ፣ ደንቦችን የመሻር ሥልጣን (በአ
ንቀጽ 82/1/ ሐ/) ይህ ሥልጣን በአንቀጽ 92/1/ ለተዘረዘሩት ዓይነት ደንቦች
ብቻ የተወሰነ ነው ብሎ አቋም መውሰድ ስህተት ነው ።

ለማጠቃለል ያህል አዋልድ ያልሆኑና እንደቀዳማዊ ሕግ የሚቆጠሩትን ደን
ቦች ለመደንገግ በሕገ መንግሥቱ ሥልጣን የተሰጠው የሚኒስትሮች ምክር ቤት
ብቻ ነው ። ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጎ የሆኑ ሌሎች የመንግሥት አካላት
እንደነኝህ ዓይነት ደንቦችን ለማውጣት ሕገ መንግሥታዊ መሠረት የላቸውም ።

አዋልድ ደንቦችን ወይም የአፈጻጸም ሕጐችን ለማውጣት እነኝህ አካሎች
ወይም እንደሚኒስትር መሥሪያ ቤት ያሉ ሌሎች አካላት በቀዳማዊ ሕግ የተሰጠ
ሥልጣን ሊኖራቸው ይችላል ። ምናልባት ጠለቅ ያለ ምርምር የሚያስፈልገውን
ችግር ቢኖር የስያሜ ጉዳይ ነው ፤ ማለትም የመንግሥት አካላት የሚያወጧቸው
አዋልድ ደንቦች ምን ስም ሊኖራቸው ይገባል ? እነኝህ ገላጭ የሆነ ስም ሊኖራ
ቸው ይችላል ፤ አዋልድ ደንቦች ወይም የአፈጻጸም ደንቦች ሊባሉ ይችላሉ ።

## መፈረም ።

መፈረም በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ አንዱ ደረጃ ነው ። መፈረም ከማጽ
ደቅ በኋላ የሚመጣ ደረጃ ሲሆን ከፊርማ በኋላ ግን ማወጅ ይቀጥላል ። መፈረም
ሥልጣን ነው እንኳ ተብሎ ቢቆጠርም እንዳስፈላጊነቱ ሊጠቀሙበት የሚቻል
ሥልጣን አይደለም ። እንዲያውም ጠባየ ነክ ነው ። ማለትም ከመፈረም በፊት ያ
ሉት ደረጃዎች መጠናቀቃቸው ከተረጋገጠ በኋላ ወዲያውኑ ሊወጡት የሚገባ ግ
ግዴታ ነው ። ከታች እንደምናየው ይህ ሁኔታ ከብዙ ሶሻሊስት ሀገሮች ሕጐችና
ልምዶች ጋር ተመሳሳይ ነው ። የአንዳንድ ሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች
አንድ የጸደቀ ሕግ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ሳይታተም ሊቆይ የሚችልበት ከፍተኛው
ጊዜ እስከመቼ ሊሆን እንደሚችል የሚገልጽ አንቀጽ አላቸው ። ለምሳሌ ያህል በአ
ልባኒያ ሕጐች በሕግ አውጪው ክፍል " ከጸደቁ በኋላ ከ15 ቀን በማይበልጥ ጊዜ
ውስጥ" በኦፊሴላዊ ጋዜጣ ላይ መታተም አለባቸው ። [5] በቡልጋሪያ ብሔራዊ
ጉባኤ የጸደቁ ሕጐች " ከጸደቁበት ጊዜ ጀምሮ ከ15 ቀን በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ"

በመንግሥት ጋዜጣ ላይ መታተም አለባቸው ። [6] ይህ ሁኔታ በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክም [7] ሆነ በሩማንያ [8] ተመሳሳይ ነው ።

ሕግን መፈረም የሚችሉት አካላት የትኞቹ እንደሆኑ በአንዳንድ አገሮች ሕገ መንግሥት በግልጽ ተጠቅሰዋል ። በሩሲያ ውስጥ “ የሶቪየት ኅብረት ሕጎች ፡ ድንጋጌዎችና ሌሎችም የሶቪዬት ኅብረት የበላይ ምክር ቤት ውሳኔዎች በበላይ ምክር ቤቱ ፕሬዚዲየም ሊቀ መንበርና ጸሐፊ ፊርማዎች በየሪፓብሊኮቹ ይታተማሉ ። [9] በሩማኒያ ሶሻሊስት ሪፑብሊክ የታላቁ ብሔራዊ ጉባኤ ሕጎች በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ይፈርማሉ ። [10] የመንግሥት ምክር ቤት ሊቀመንበርና ጸሐፊ በሴይም ( የፖላንድ ሕዝባዊ ጉባኤ ) የሚወጡትን ሕጎች ይፈርማሉ ። [11] በኩባ በብሔራዊ ጉባኤው የጸደቁትን ሕጎች የመፈረም ኃላፊነት የተሰጠው ለሕዝባዊ ኃይል ብሔራዊ ጉባኤ ፕሬዚዳንት ነው ። [12] በሀንጋሪ ፓርላማ የተላለፉት ሕጎች የሚፈረሙት በሀንጋሪ ሕዝባዊ ሪፓብሊክ ፕሬዚዲየም ሊቀ መንበርና ጸሐፊ ነው ። [13]

በዚህ ጉዳይ ላይ የኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት ምንም ነገር አይገልጽም ። ምናልባት ትንሽ ፍንጭ ቢኖር ከአንቀጽ 86/5/ በመነሳት ይሆናል ። ይህን ነገር በተመለከተ ይህ አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል ።

> የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ፕሬዚዳንት በዚህ ሕገ መንግሥትና በሌሎችም ሕጎች መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ።
>
> በብሔራዊ ሸንጎ ፡ በመንግሥት ምክር ቤትና በሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚወጡትን ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ ማወጅ ።

በሕዝባዊ ጉባኤ የወጡትን ሕጎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ መፈረምና እነዚሁ ሕጎች በኦፊሴላዊ ጋዜጣ እንዲታተሙ መፈረም ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው ። የመጀመሪያው ተግባር የሚከናወነው (በተለይ በሁሉም ሶሻሊስት አገሮች) በጉባኤው ሰብሳቢ አማካይነት ነው ። የኋለኛው የሚከናወነው ግን በመንግሥት ምክር ቤት ፕሬዚዲየም ሊቀ መንበር አማካይነት ነው ።

ሕግን በነጋሪት ጋዜጣ ማወጅና ሕግን መፈረም የተገናኙ ነገሮች በመሆናቸው ከአንቀጽ 86/5/ በመነሳት በብሔራዊ ሸንጎ ፡ በመንግሥት ምክር ቤትና በፕሬዚዳንቱ የሚወጡ ሕጎች በፕሬዚዳንቱ (ማለትም የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት) ይፈረማሉ የሚል አስተያየት መስጠትና መከራከር ትክክለኛ ነው ።

ይህ ሁኔታ ስለመፈረም ጉዳይ ከፊል መልስ ሊሆን ይችላል ። በአንቀጽ 86/5 እና ከላይ በቀረበው ሀሳብ መሠረት የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት የመንግሥት ምክር ቤት የሚያወጣቸውን ድንጋጌዎችና ልዩ ድንጋጌዎች እንዲሁም ራሱ የሚያወጣቸውን ድንጋጌዎችና ልዩ ድንጋጌዎች ብቻ ይፈርማል ። በዚህ አንቀጽ የመጀመሪያ ክፍል እንደ ተጠቀሰው በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጡ ደንቦችና በበላይ ሕግ መብት በተሰጣቸው አካሎች የሚወጡ አዋልድ ደንቦች አሉ ። ፕሬዚዳንቱ በነጋሪት ጋዜጣ የሚያውጃቸው ሕጎች በሕገ መንግሥቱ የተዘረዘሩ በመሆናቸው ፕሬዚዳንቱ ሌሎች ዝቅተኛ አካሎች የሚያወጣቸውን ሕጎች ይፈርም ማለት የማይጣጣም ሀሳብ ስለሚሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጡትን ደንቦች ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀ መንበር ነውና ፡ እንዲፈርምባቸው ፡ እንዲሁም አዋልድ ደንቦችን ለማውጣት መብት የተሰጠው አካል የሚያወ

ጣቸውን ደንቦች የዚህ አካል የበላይ ኃላፊ እንዲፈርምባቸው ቢደረግ አግባብ ነው ብዬ አምናለሁ ።

## በነጋሪት ጋዜጣ ማሳተም

በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ የመጨረሻው ደረጃ የተደነገጉትን ሕጎች ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ ጋዜጣ ላይ ማሳተም ነው ። የዚህ ሂደት ደረጃ አጠቃላይ ዓላማ ሕጎችን ኅብረተሰቡ ወይም ሕዝቡ እንዲያውቃቸው ለማድረግ ነው ።

ሕጎችን በጋዜጣ ማሳተም ልክ ሕጎችን እንደመፈረም ሁሉ ሁልጊዜም ያለ ማቋረጥ መደረግ ያለበት ነው ። ምክንያቱም በጋዜጣ ማሳተም ሥልጣን ሳይሆን የሕግ አወጣጥ ሂደት አንዱ አካል ነውና ። ይህንን ኃላፊነት የወሰደው አካል ሕጉ በትክክለኛው አካል መደንገጉንና መፈረሙን ካረጋገጠ በኋላ ለዚሁ ሲባል በተቋቋመ ጋዜጣ አማካይነት ያውጃል ።

በጋዜጣ ማሳተም ሕጎች ለታተመባቸው ጋዜጦችና ለእያንዳንዱም የሕግ ዓይነት ተከታታይ ቁጥር መስጠትን ያካትታል ።

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት መሠረት ሕጎች በአንድ አካል ወይም በአንድ ግለሰብ አማካይነት ብቻ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ አይታተሙም ። የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት " በብሔራዊ ሸንጎ ፣ በመንግሥት ምክር ቤትና በሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚደነገጉትን ሕጎች "[14] በነጋሪት ጋዜጣ ያውጃል ። ይህ ደግሞ አዋጆችን ፣ የመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌዎችና ልዩ ድንጋጌዎችን ፣ የፕሬዚዳንቱን ድንጋጌዎችን ና ልዩ ድንጋጌዎችን ጭምር ያካትታል ። ነገር ግን ቀደም ሲል ካየነው የሕጎች ዝርዝር ውስጥ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጡ " ሕገ—ደንቦች " እና መብት በተሰጣቸው የመንግሥት አካላት የሚወጡ አዋልድ ሕጎች ወይም የአፈጻጸም ደንቦች ይገኙበታል ። ስለዚህ እነኝህ ሕጎችና ደንቦች እንደሌሎቹ ሕጎች ሁሉ በነጋሪት ጋዜጣ መታተም ይኖርባቸዋል ። ከዚህ ጋር በማያያዝ እነኝህን ደንቦች በነጋሪት ጋዜጣ የሚያውጃቸው ማነው የሚለው ጥያቄ ይከተላል ። ለዚህ ጥያቄ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የሚሰጠው መልስ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሚደነገጉ ሕጎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፣ በመንግሥት አካሎች ለሚወጡ የአፈጻጸም ደንቦች ደግሞ የነኝህ አካሎች ተጠሪዎች ያውጃሉ የሚል ይሆናል ።

በደረጃ ቀደም ተከተል ሲታዩ አብዛኛቹ ሕጎች በአዋጅ ፣ በመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌና በፕሬዚዳንት ድንጋጌ መልክ ስለሚወጡ ነጋሪት ጋዜጣው እነኝህን ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ ለማወጅ ሥልጣን በተሰጠው በሪፓብሊክ ፕሬዚዳንት ቢሮ ሥር ቢተዳደር የተሻለ ይሆናል ።

## ክለሳና ቅንብር

በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ የክለሳና የቅንብር ደረጃ ከማመንጨት ደረጃ ቀጥሎ የሚመጣ ደረጃ ነው ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ይህን ጉዳይ ወደኋላ እንዲመጣ ያደረግሁት ይኸው የጽሑፍ የመጨረሻ ክፍል አስተያየቶችን የያዘ ክፍል በመሆኑ ነው ።

ለጥናታችን የተመረጡትን አንዳንድ አገሮች ልምድ ከመመርመራችን በፊት ክለሳና ቅንብር ራሱ ምንን እንደሚያካትት ባጭሩ ለመመልከት እንሞክራለን ። በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ ይህ ደረጃ ሲደረስ እያንዳንዱ ረቂቅ ሕግ በሚከተሉት አንጻር ይመረመራል ፣ እንዲሁም ይገመታል ።

1. ከሕገ መንግሥቱ ፡ (ከፓርቲ) ከመንግሥት ፓሊሲና ዕቅድ ጋር አለመቃረኑ ፤
2. ከሕግ ማርቀቅ ቴክኒክና የሕጐች መርህ ጋር መጣጣሙ
3. ለእያንዳንዱ የሕግ ዓይነት ከተቀመጠው ቅርጽ ጋር መጣጣሙ
4. በሕጉ ውስጥ ውስጣዊና ውጫዊ ቅራኔዎች መጥፋታቸውና
5. ረቂቅ ሕግ ሊያስወግድ የፈለገውን ችግር ማቃለል የሚችሉ አንቀጾች መኖራቸውን ማረጋገጥ ።

በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያልፍ ማንኛውም ረቂቅ ሕግ ያለምንም ማመንታት ሁሉም ባይሆኑም አብዛኞቹ ስህተቶቹ ይወገዳሉ ።

ስለዚህ ጠቃሚ የሕግ አወጣጥ ደረጃ ጉዳይ ከሌሎች አገሮች ልምድ ለማወቅ መጣር በትምህርታዊነቱ ብቻ ሳይሆን ለፖሊሲ አውጪዎችም በጣም ጠቃሚ ነው ፖላንዶች እላይ የተጠቀሱትን ተግባሮች የሚያከናውን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቢሮ ውስጥ የሚገኝ የሕግ ኮሚሽን አላቸው ።[15] በፈረንሳይ ክለሳና ቅንብር በካውንስል ዴኤታ [16] ሲካሄድ በፌዴራል ጀርመን ግን ይህ ተግባር በፍትህ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ይሟላል ።[17]

በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥት የረቂቅ ሕጐችን ክለሳና ቅንብር ያከናውን የነበረው የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ ኮሚቴ ነበር ።[18] እያንዳንዱ ሕግም የሚመነጨው ወይም የሚያልፈው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ነበር ።

በኢሕዲሪ መንግሥት ሁኔታው የተለየ ነው ። ቀደም ሲል እንደዓየነው ሕጐች ቀጥታ ተጠሪነታቸው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ካልሆነ አካሎች ይመነጫሉ ። ይህ ሁኔታ የሚኒስትሮችን ምክር ቤት ሕግ ኮሚቴ መብት እንዳይኖረው ስለሚያደርገው የሁሉንም ሕጐች የክለሳና የቅንብር ተግባር እንዳያሟላ ያደርገዋል ። በአዲሱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አወቃቀር የዚህ ኮሚቴ ህልውና እንደሚቀጥል አድርገን ብንገምት ከዚህ አካል የሚወጡት ሕጐች ምናልባት በበፊት ሁኔታ ሊከለሱና ሊቀናበሩ ይችላሉ ።

ይህ ሁኔታ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 71 የተዘረዘሩት ቀሪዎቹ በስምንት አካሎች የሚያመነጩቸውን ረቂቅ ሕጐች እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የክለሳና የቅንብር ተግባር የሚያከናውን አካል አልባ ያደርጋቸዋል ። ከእነኝህ ስምንት አካላት የሚወጡትን ሕጐች ለመከለስና ለማቀናበር የሚችል አካል መፍጠር ይቻላል ። ነገር ግን በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ አስተያየት በአሁኑ ሰዓት በአገሪቱ ውስጥ ካለው የሕግ ባለሙያዎች እጥረት አኳያ ሲታይ አለአስፈላጊና ከአቅም በላይ ሆኖ ይታያል ። በተጨማሪም ሌላ የክለሳና የቅንብር ማዕከል እንዲኖር ማድረግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ ኮሚቴ (ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሚመነጩ ሕጐች) እና ሌላው አቀናባሪ አካል (በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 71 ከተዘረዘሩት ስምንት አካላት ለሚወጡ ሕጐች) የከለሷቸውንና ያቀናበራቸውን ሕጐች እንደገና መከለስና ማቀናበር በሚያስፈልግበት ጊዜ ሌላ አንድ ተጨማሪ አቀናባሪ እንዲኖር ግድ የሚል ይሆናል ።

ይህ ሁኔታ ደግሞ ሕግ አውጪ ማዕከልን የማቋቋምና ሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ ኮሚቴን ማፍረስ ያሻል ወደሚል ሀሳብ ያመራናል ። በዚህ ሕግ አውጪ ማዕከል ተነጻጻሪ እጩዎች የሚከተሉት ይሆናሉ ።

- የመንግሥት ምክር ቤት
- የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት ቢሮ
- የሚኒስትሮች ምክር ቤትና
- የፍትህ ሚኒስቴር

የመንግሥት ምክር ቤት የሕግ ማውጣት ተግባሮችን በሚመለከት ረገድ ዋነኛ ማዕከል ነው ። የመንግሥት ምክር ቤት የብሔራዊ ሸንጎው ቋሚ አካል መሆኑ ፣ ከፍተኛው ሕግ አውጪ አካል መሆኑ ፣ ድንጋጌዎችን የማውጣት ሥልጣኑ ፣ ሕገ መንግሥቱንና ሌሎች ሕጎችን መተርጐም ከመቻሉ ጋር ተጣምሮ ፣ እንዲሁም ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጎ የሆኑ የመንግሥት አካሎች የሚያወጧቸውን ደንቦችና መመሪያዎች የመሻር ሥልጣኑን ስንመለከት የመንግሥት ምክር ቤት ሕግ አውጪ ማዕከል ይሁን ለሚለው ሀሳብ በቂ ድጋፍ ከሚሰጡት ምክንያቶች ዋነኞቹ ናቸው ።

የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት ቢሮ ሕግ አውጭ ማዕከል ይሁን የሚለው ሀሳብ የሚነሳው በአመዛኙ በሁለት ምክንያቶች ነው ። አንደኛው ድንጋጌ ለማውጣት ፕሬዚዳንቱ ሥልጣን ያለው መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አዋጆችን ፣ የመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌዎችንና ልዩ ድንጋጌዎችን ፣ የፕሬዚዳንቱ ድንጋጌዎችንና ልዩ ድንጋጌዎችን በነጋሪት ጋዜጣ የማወጅ ኃላፊነት የተሰጠው የፕሬዚዳንቱ ቢሮ በመሆኑ ነው ።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሕግ አውጪ ማዕከል ይሁን ለሚለው ሀሳብ ምክንያት የሚሆነው በዚህ አካል ሊመነጩ የሚችሉት ሕጎች ብዛት ስላላቸው ብቻ ነው ። አብዛኞቹ የመንግሥት ተግባሮች የሚከናወኑት በሚኒስትር መሥሪያ ቤቶችና በሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት አካሎች ስለሆነ በአዋጅ ፣ በመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌዎች ፣ በፕሬዚዳንቱ ድንጋጌዎች ደንቦች መልክ የሚወጡት ሕጎች በጣም በብዛት የሚወጡት ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው ። ደንቦችን ለመደንገግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያለውን ሥልጣን ደግሞ ካየን ይህን አቋማችንን የሚደግፍ ነው ።

ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ መጨረሻ ላይ የተጠቀሰው እጩ የፍትህ ሚኒስቴር ነው ። ለሕግ አውጪ አካልነት ይህን ሚኒስቴር የምናጨው አስፈላጊው የባለሙያ ኃይል በበቂ ሁኔታ ይገኝበታል የሚለውን ግምት በመውሰድ ነው ።

ከላይ በቀረበው ትንታኔና በግልጽ እንደሚታየው ሕግ አውጪ ማዕከል የመንግሥት ምክር ቤት መሆን አለበት ወደሚል ማጠቃለያ ያመራናል ።

ረቂቅ ሕጎች ከተለያዩ ምንጮች ወደ ሕግ አውጪው ማዕከል መላካቸውና ሕግ በማርቀቅ ሂደት ውስጥ ያለውን ውስብስብነትና ቴክኒክ ልብ ካልን በኋላ በኔ በኩል የምሰጠው አስተያየት ማናቸውም ረቂቅ ህጎች ወደሚደነግጋቸው አካል ከመሄዳቸው በፊት እነኝህኑ ረቂቆች የሚከልልና የሚያቀናብር ኮሚቴ መቋቋም አለበት የሚል ይሆናል ። ኮሚቴው የተወከለና የሕግ ማርቀቅ ውጣ ውረድ በደንብ የሚያውቅ መሆን አለበት ።

የኮሚቴው አባሎች ከሚከተሉት ቢውጣጣ የተሻለ ይሆናል ።

- ከመንግሥት ምክር ቤት
- ከፍትህ ሚኒስቴር
- ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ
- ለሚረቀቀው ሕግ ኃላፊነት የወሰደው አካል
- ስለሕግ ማርቀቅ ጥሩ ዕውቀት ያላቸው ከ3 የማይበልጡ ግለ ሰቦች

## የግርጌ ማስታወሻ ፤

* በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሕግ መምሪያ ኃላፊ ፡ ኤል ኤል ቢ ፣ ሕግ ፋኩልቲ አ. አ. ዩ. (ቀ.ኃ.ዩ.) ኤል ኤል ኤም ፡ (ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ) ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ፋኩልቲ በትርፍ ጊዜ አስተማሪ ።


1. የኢሕዲሪ ሕግ መንግሥት አንቀጽ 63 ።
2. ከዚያው ጠቀሳ ፡ አንቀጽ 82/3/ ።
3. ከዛው ጠቀሳ ፡ ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ 86/4/ ።
4. ይህ ጉዳይ በአንድ ወይም በሁለት ፓራግራፎች ብቻ የሚጠቃለል አይደለም። የሕግ መንግሥቱ አንቀጽ 83 ከብዙ አጨቃጫቂ አንቀጾች አንዱ ከመሆኑም በላይ ሕገ መንግሥትን የሚያጠኑ ተመራማሪዎች ብዙ ምርምር እንዲያካሂዱበት የሚጠይቅ ነው ።
5. የአልባኒያ ሕዝብ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት ፡ አንቀጽ 74 ።
6. የቡልጋሪያ ሕዝብ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84/1/ ።
7. የጀርመን ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 65/5/ ።
8. የሮማኒያ ሶሻሊስት ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 57 ።
9. የዩ.ሶ. ሶ. ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 116 ።
10. የሩማኒያ ሶሻሊስት ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 57 ።
11. የፖላንድ ሕዝብ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 25/2/ ።
12. የኩባ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79/ዲ/ ።
13. የሀንጋሪ ሕዝባዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 26 ።
14. የኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 87/5/ 1/ ።
15. አር አርዘቭስኪ ፡ “ ዘ ሲስተም ኤንድ ሞድ ኦፍ ክሪኤቲንግ ሎው ኤንድ ዘ ፓሊሽ ፒፕልስ ሪፓብሊክ ” “ዘ ሎው ኢን ፖላንድ ” ፡ (1978) ከገጽ 7-38
16. ደብሊዩ ዲል ፡ ሌጂስሌቲቭ ድራፍቲንግ ፣ ኤኒው አፕሮች ፡ ከገጽ 334-335
17. ከላይ የተጠቀሰው
18. ሺፈራው ወ/ሚ ፣ በዚሁ እርእስት “ ክፍል አንድ ፡ የሕግ አወጣጥ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት ” እላይ ገጽ — ተመልከት ።